# ለ MAP Growth የቤተሰብ መመሪያ

እያንዳንዱ ተማሪ ስለሚያውቀው እና በሚቀጥለው ምን ለመማር ዝግጁ እንደሆነ አስተማሪዎች ሲያውቁ ልጆች በተሻለ እና በፍጥነት ይማራሉ። የአስተማሪ እና ተመራማሪዎች ቡድን NWEA® ን - በጣም የታመኑ እና አስተማማኝነታቸው የተረጋገጠ የግምገማ መፍትሄዎችን የፈጠረ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት - ያቋቋሙት። በአሜሪካ እና በዓለም ዙሪያ ከ 140 በላይ አገሮች ውስጥ ከ 11 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች የ MAP® Growth™ ይጠቀማሉ፡፡

## እንዴት እንደሚሰራ

MAP Growth የኮምፒተር ማስተካከያ ፈተና ነው፡፡ ልጅዎ አንድን ጥያቄ በትክክል ከመለሰ የሚቀጥለው ጥያቄ የበለጠ ፈታኝ ነው። በተሳሳተ መልስ ከሰጡ ቀጣዩ ቀላል ነው። የእንደዚህ ዓይነቱ ግምገማ ችሎታቸው ከክፍል ደረጃቸው በታች የሆኑ ተማሪዎችን ሳያደናግጥ ከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን ተማሪዎች ይፈትናል።




የ MAP Growth የእያንዳንዱ ተማሪ የክፍል ደረጃ በሚመጥን ጥያቄ ይጀምራል እና በእያንዳንዱ የተማሪ ብቃት ደረጃን መሰረት በማድረግ የከባድነት ደረጃን ያስተካክላል።

## ምን እንደሚለካ

MAP Growth የትምህርት ደረጃቸው ምንም ይሁን ምን ተማሪዎች ምን እንደሚያውቁ በትክክል ለመለካት የ RIT መለኪያ ይጠቀማል። እንዲሁም የልጆችን እድገት በጠቅላላው የትምህርት ዓመት እና በበርካታ ዓመታት ውስጥ ለመከታተል እንዲችሉ በማድረግ በጊዜ ሂደት ለውን እድገት ይለካል። ልጅዎ የ MAP Growth ፈተናን አንዴ ከጨረሰ በኋላ የ RIT ውጤት ያገኛል።




የ RIT መለኪያው የተማሪ ብቃትን በትክክል ይለካል፤ ምንም እያከናወኑ ቢሆኑም፣ በክፍል ደረጃቸው፣ ከዛ በላይ ወይም በታች።

## የልጅዎ የ RIT ውጤት

በክፍል ደረጃዎች ሁሉ የ RIT ውጤቶች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። የአራተኛ ክፍል ተማሪ እና የስምንተኛ ክፍል ተማሪ በንባብ ተመሳሳይ RIT ውጤት ካላቸው በዛ ትምህርት በተመሳሳይ ደረጃ እየሞከሩ ነው፡፡ ይህ የተመጣጠነ ልኬት አስተማሪዎች የእያንዳንዱን ተማሪ የትምህርት ዕድገት በትምህርት ዓመቱ በሙሉ እና በጊዜ ሂደት በትክክል ለመለካት ያስችላቸዋል።

የልጆዎን ግብ ለማሳካት የ RIT ውጤታቸውን መጠቀም ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች የትኛውን ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች ለመግባት በሂደት ላይ እንዳሉ ለማየት የራሳቸውን RIT ውጤቶች ወደ ኮሌጅ አሰሳ መሳሪያችን ውስጥ ማስገባት ይችላሉ። እንዲሁም ለተማሪዎች መጽሐፍት ለመጠቆም እና ድህረ-ገጽ ተኮር የሆኑ መልመጃዎች ለመስጠት ለምሳሌ YourReadingPath.com እና KhanAcademy.org የ RIT ውጤቶችን የሚጠቀሙ የኦንላይን መጽሀፎችን ማየት ይችላሉ።

> "የ MAP Growth አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ምን ያህል እንደማውቅ እና የመቶኛ እድገቴን ለእኔ እና ለአስተማሪዬ እንድንመለከት ያስችለናል፡፡ በሂሳብ ውጤቴ 227 ነበር (70ኛ መቶኛ) ግን አሁን 240 (87ኛ መቶኛ) ነው፡፡ በጣም ብዙ እድገትን ማሳየት እንደምችል አላውቅም ነበር ግን በመጨረሻ እድገቱን አሳየሁ።"
>
> Kayla፣ 6ኛ ክፍል
> Santa Ana, CA

### የተለመዱ ጥያቄዎች

| | |
|---|---|
| **ት/ቤቶች እና አስተማሪዎች የ MAP Growth ውጤቶችን እንዴት ይጠቀማሉ?** | አስተማሪዎች ትምህርቱን ለማስተማር፣ ትምህርትን ግላዊ ለማድረግ እና የእያንዳንዱን ተማሪ እድገት ለመቆጣጠር ውጤቱን ሊጠቀሙ ይችላሉ። ርእሰመምህር እና አስተዳዳሪዎች የክፍል ደረጃን፣ ት/ቤቱን ወይም አጠቃላይ ወረዳውን ብቃት እና መሻሻል ያለበትን ቦታ ለማየት ውጤቶቹን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ |
| **ልጄ በክፍል ደረጃ ላይ እየሠራ መሆኑን የ MAP Growth ሊነግረኝ ይችላልን?** | አዎ፣ ግን እባክዎን ያስታውሱ የ MAP Growth ውጤቶች አስተማሪዎች ተማሪን እንዴት እያከናወነ እንዳለ ለማወቅ የሚጠቀሙበት አንድ የመረጃ ነጥብ ብቻ ነው፡፡ እባክዎን ስለ ልጅዎ ብቃት ማንኛውንም ጥያቄዎች ካሉዎት ከአስተማሪቸው ጋር ይወያዩ፡፡ |
| **ልጄ MAP Growth ፈተናዎችን ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?** | አብዛኞቹ ት/ቤቶች በትምህርት አመት መጀመሪያ፣ መሀከለ እና መጨረሻ (በመኸር ፣ በክረምት እና በፀደይ) ላይ ለተማሪዎች የ MAP Growth ፈተናዎችን ይሰጣሉ። አንዳንድ ትምህርት ቤቶች በዓመት ሁለት ጊዜ ብቻ ፈተናዎችን ለማካሄድ ይመርጣሉ፡፡ |
| **ህጎች ምንድን ናቸው?** | NWEA በ US ዙሪያ ከ 10 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎችን ማንነቱ ያልታወቀ መረጃን በመጠቀም ለት/ቤቶች ደንቦችን ያወጣል፡፡ የእነዚህ ተማሪዎች የተጣመረ ከፍተኛ ፣ የመካከለኛ እና የታችኛው ውጤት ማወቁ መምህራን ልጅዎ ከሌላው ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸር የት እንዳለ ለማነጻጸር እና እንዲያድጉ ለመርዳ ያስችላቸዋል፡፡ በተጨማሪም NWEA ከ US ውጭ ለ MAP Growth የሚጠቀሙ የግል፣ ዕውቅና ላላቸው፣ እንግሊዝኛ-ተኮር፣ ዓለም አቀፍ ት/ቤቶች የማነጻጸሪያ መረጃ ያቀርባል፡፡ |
| **የ MAP Growth ደረጃውን የጠበቀ ፈተና ነው?** | የ MAP Growth በትምህርት ዓመቱ ወቅት በተወሰነ ጊዜ ይሰጣል፡፡ ሁሉንም ተማሪዎች ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ከመጠየቅ ይልቅ ለእያንዳንዱ ልጅ እውቀት የበለጠ ትክክለኛ ልኬት በመስጠት የእያንዳንዱ ልጅ ብቃት ያስተካክላል። አስተማሪዎች ወዲያውኑ ውጤቶችን ይቀበላሉ፣ ይህም በፍጥነት ምላሽ እንዲሰጡ ያስችላቸዋል። |
| **በ MAP Growth ፈተናዎች ላይ ምን ዓይነት ጥያቄዎች አሉ?** | የ MAP Growth ፈተናዎች የመልስ ምርጫ ያላቸው ጥያቄዎችን፣ መጎተት እና መጣል እንዲሁም ሌሎች የጥያቄ አይነቶችን ያጠቃልላል፡፡ ለሙከራ ፈተና Warmup.NWEA.org ይመልከቱ፡፡ |

**ለ MAP Growth ፈተና ለመዘጋጀት ምክር ለማግኘት ብሎጋችንን ይመልከቱ፡**
**nwea.org/blog/category/supporting-families/**
**nwea.org/familytoolkitላይ ተጨማሪ የቤተሰብ መጽሄቶችን ያግኙ፡፡**

nwea

NWEA የግምገማ መፍትሄዎችን፣ መረጃ ያዘሉ ሪፖርቶችን፣ የሙያ መማሪያ እድሎችን እና የምርምር አገልግሎቶች የሚሰጥ በአለማቀፍ ዙሪያ ለተማሪዎች እና አስተማሪዎች ድጋፍ የሚያደርግ ለትርፍ-ያልተቋቋመ ድርጅት ነው፡፡ ሁሉም ልጆች እንዲማሩ ለማገዝ NWEA ከእርስዎ ጋር እንዴት እንደሚጣመር ለማወቅ NWEA.org ይጎብኙ፡፡

© 2019 NWEA. NWEA እና MAP የተመዘገቡ የንግድ ምልክቶች ናቸው፤ US እና ሌላ አገሮች ወስጥ MAP Growth የ NWEA የንግድ ምልክት ነው፡፡
Illustrations © Adam Simpson and Heart 2017 የተጠቀሱ የሌሎች ኩባንያዎች ስሞች እና ምርቶቻቸው የባለቤቶቻቸው የንግድ ምልክቶች ናቸው፡፡